# የብልጽግና ፓርቲ አመራር ምደባ

# አፈፃፀም መመሪያ

## ቁጥር 11/2015

**የካቲት 2015**

**አዲስ አበባ**

# ማውጫ


ገጽ

ክፍል አንድ .......... 2

ጠቅላላ ድንጋጌዎች .......... 2

ክፍል ሁለት .......... 5

የአመራር መደቦች .......... 5

ክፍል ሦስት .......... 7

የአመራር ምደባ ሥርዓት .......... 7

ክፍል አራት .......... 13

የአመራር ምደባ መስፈርቶች .......... 13

ክፍል አምስት .......... 19

አመራር ከኃላፊነት ስለሚነሳበትና የቅሬታ አቀራረብ ሥርዓት .......... 19

ክፍል ስድስት .......... 21

ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች .......... 21

# የብልጽግና ፓርቲ አመራር ምደባ አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 11/2015

## <u>መግቢያ</u>

አሁን በሥራ ላይ ያለው የብልጽግና ፓርቲ የአመራር ምደባ ሥርዓት የፖለቲካ አስተሳሰብ፣ የአመራር ብቃት፣ ሥነ-ምግባር፣ ተመጣጣኝ ውክልና እና የምደባ ቦታዎች ልዩ ባህሪ መካከል ሚዛን ለመጠበቅ በበቂ ሁኔታ የሚያስችል ባለመሆኑ፣

ግልጽ፣ ፍትሓዊና ውጤታማ የአመራር ምደባ ሥርዓት መዘርጋት ፓርቲንና መንግስትን ሳይንሳዊ፣ ዴሞክራሲያዊና ህግና ስርዓትን መሰረት ባደረገ መልኩ ለመምራትና ተቋም ለመገንባት፣ አገራዊ ግንባታን ለማፋጠንና የሕዝብ ቅቡልነትን ለማግኘት አስፈላጊ በመሆኑ፣

የብልጽግና ፓርቲ የአመራር ምደባ ሥርዓት አሳታፊ፣ ግልጽ በሆኑ መርሆዎች፣ መስፈርቶችና ሂደቶች የሚመራና ተጠያቂነትን የሚያሰፍን እንዲሆን ማድረግ የውስጥ ፓርቲ ዴሞክራሲን፣ መተማመንና አንድነትን ለማጠናከርና የፓርቲ ቀጣይነት ለማረጋገጥ አስፈላጊ በመሆኑ፣

የብልጽግና ፓርቲ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ በመተዳደሪያ ደንቡ አንቀጽ 19 ንዑስ አንቀጽ 6(ሸ) መሠረት ይህን የአፈፃፀም መመሪያ አውጥቷል፡፡

# ክፍል አንድ

# ጠቅላላ ድንጋጌዎች

## <u>አንቀጽ 1</u>

## አጭር ርዕስ

***ይህ መመሪያ "የብልጽግና ፓርቲ የአመራር ምደባ አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር*** 11/2015"
ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## <u>አንቀጽ 2</u>

## ትርጓሜ

በዚህ መመሪያ ውስጥ የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በቀር

1. **"መተዳደሪያ ደንብ"** ማለት የብልጽግና ፓርቲ መተዳዳሪያ ደንብ ማለት ነው፡፡
2. **"የፓርቲ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ"** ማለት የብልጽግና ፓርቲ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ማለት ነው፡፡
3. **"ፕሬዚንዳንትና ምክትል ፕሬዚዳንቶች"** ማለት የፓርቲው ፕሬዚዳንትና ምክትል ፕሬዚዳንቶች ናቸው፡፡
4. **"የፌደራልና የክልል ፓርቲ አመራሮች የጋራ መድረክ"** ማለት በመተዳደሪያ ደንቡ አንቀጽ 20 መሰረት የፌደራልና የክልል አመራሮችን በማካተት የተደራጀ የፓርቲው የአመራር መድረክ ነው፡፡
5. **"አስተባባሪ ኮሚቴ"** ማለት በየደረጃው የፓርቲና የመንግስት ሥራዎችን አቀናጅቶ በበላይነት የሚያስተባብር እና የሚመራ የፓርቲው አደረጃጀት ነው።
6. **"የፓርቲ ጽ/ቤት የሥራ አመራር ኮሚቴ"** ማለት በየደረጃው የሚገኙ የፓርቲ ጽህፈት ቤቶችን ሥራዎች እንዲመሩና እንዲያስተባብሩ የተመደቡ አመራሮች ስብስብ ነው፡፡
7. **"የፓርቲ ዋና ጽ/ቤት"** ማለት የብልጽግና ፓርቲ ዋና ጽህፈት ቤት ነው፡፡
8. **"የፓርቲ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቶች"** ማለት በመላው ሀገሪቱ ከክልል እስከ ቀበሌ ባሉ መዋቅሮች የፓርቲ ስራ እንዲሰሩ፣ እንዲመሩና እንዲያስተባብሩ የሚቋቋሙ የብልጽግና ፓርቲ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቶች ማለት ነው።

9. **"የፌደራል ተቋማት"** ማለት የሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት፣ የፌዴሬሽን ም/ቤት፣ ሚኒስቴር መ/ቤቶች፣ ኮሚሽኖች፣ ባለስልጣኖች፣ ኤጀንሲዎች፣ ኢንስቲትዩቶችና የመሳሰሉ የፌደራል መንግስት አካላን ያጠቃልላል።
10. **"አመራር"** ማለት ከቀበሌ እስከ ፌዴራል ባለ የመንግስትና የፓርቲ መዋቅር ላይ በኃላፊነት የሚመደብ አመራር ነው፡፡
11. **"የአመራር እርከን"** ማለት ከቀበሌ እስከ ፌዴራል በተመሳሳይ የኃላፊነት ማዕረግ ወይም ደረጃ ላይ ያሉ የመንግስትና የፓርቲ የኃላፊነት መደቦች (ጠቅላይ ሚኒስትር፣ ር/መስተዳድር፣ ሚኒስትር፣ ሚኒስትር ዴኤታ፣ አፈ-ጉባኤ፣ ቢሮ ኃላፊ፣ የመሳሰሉ) ናቸው፡፡
12. **"አባል"** ማለት የብልጽግና ፓርቲ አባል ማለት ነው፡፡
13. **"ፕሮፋይል"** ማለት የእጩ አመራሩን የግል መረጃ፣ የሥራ ልምድ፣ የትምህርት ዝግጅት፣ የሥራ አፈፃፀም፣ የሥነ-ምግባር እና የአመራርና የፖለቲካ ብቃት ሁኔታ የያዘ ሰነድ ነው፡፡
14. **"የአመራር ቋት"** ማለት በአመራርነት የተመደቡ ወይም ሊመደቡ የሚችሉ በግንባር ቀደምነት መስፈረት ተለይተዉ የተያዙ የፓርቲ አባላትን ፕሮፋይል የያዘ የመረጃ ቋት ነው፡፡
15. **"ክልል"** ማለት በህገ መንግሥቱ አንቀጽ 47 መሠረት የተቋቋመ ክልል ሲሆን ለዚህ መመሪያ አፈፃፀም ሲባል የአዲስ አበባ እና የድሬዳዋ አስተዳደርን ይጨምራል።
16. **"ዞን"** ማለት ልዩ ወረዳዎችን፣ በአዲስ አበባ ከተማ የሚገኙ ክፍለ-ከተማዎችንና ለክልል ተጠሪ የሆኑ ከተሞችን ጨምሮ ከክልል ቀጥሎ የሚገኝ የአስተዳደር እርከን ነው፡፡
17. **"ወረዳ"** ማለት አግባብነት ባለው ሕግ መሠረት ሥልጣን በተሰጠው አካል የወረዳ ደረጃ የተሰጠው የአስተዳደር እርከን ሲሆን ለዚህ መመሪያ አፈፃፀም ሲባል የድሬደዋ አስተዳደር የከተማ ቀበሌ እና የገጠር ክላስተር መዋቅሮችን ይጨምራል፡፡
18. **"ከተማ"** ማለት አግባብነት ባለው ሕግ መሠረት ሥልጣን በተሰጠው አካል የከተማ ደረጃ የተሰጠው የአስተዳደር እርከን ነው፡፡
19. **"ቀበሌ"** ማለት አግባብነት ባለው ሕግ መሠረት ሥልጣን በተሰጠው አካል የከተማ ወይም የገጠር የቀበሌ ደረጃ የተሰጠው የአስተዳደር እርከን ነው፡፡

20. **"ብልሹ አሰራር"** ማለት ህግና የአሠራር ስርዓትን በግልጽ ያልተከተሉ ወይም የሚጥሱ እንዲሁም ተቋምን ለኪሳራ የሚዳርጉ ወይም ውጤታማነቱን የሚጎዱ ወይም ለሙስናና ለሌብነት በር የሚከፍቱ ሂደቶች፣ ውሳኔዎች፣ ተግባራትና አሰራሮችን ያጠቃልል።
21. **"ወጣት"** ማለት እድሜው ከ18 - 35 ዓመት የሆነ ሰው ነው፡፡
22. በዚህ መመሪያ ውስጥ በወንድ ፆታ የተገለፀው የሴት ፆታንም ይመለከታል፡፡

## <u>አንቀጽ 3</u>

## ዓላማ

የመመሪያው ዓላማ በየደረጃው በፓርቲና በመንግስት መዋቅር የሚካሄደው የአመራር ምደባ ሥርዓት ግልጸኝነት የተሞላበት፣ ወጥነት ያለው፣ የተቋም ግንባታን ታሳቢ ያደረገ፣ በብቃትና በብዝሃነት መካከል ሚዛን የጠበቀ እና ተጠያቂነትን ያረጋገጠ ሆኖ እንዲከናወን በማድረግ የፓርቲውን ውጤታማነትና የአመራር ቀጣይነት ማረጋገጥ ነው፡፡

## <u>አንቀጽ 4</u>

## መርሆዎች

በዚህ መመሪያ መሠረት የሚከናወነው የአመራር ምደባ በሚከተሉት መርሆዎች ይመራል፡፡

1. የአመራር ምደባን ውጤታማ ለማድረግ በየትኛውም ደረጃ የሚካሄድ የአመራር ምደባ ሂደቱ ግልጽ፣ አሳታፊ እና ዴሞክራሲያዊ በሆነ አግባብ መከናወን ይኖርበታል፡፡
2. አንድ የፓርቲ አባል ወደ አመራርነት የሚመጣው በሚሰጠው ተልዕኮዎች ውጤታማነቱ ተረጋግጦ በአመራር ቋት ውስጥ ሲያዝና ለቦታው የተቀመጠውን መስፈርት የሚያሟላ መሆኑ ሲረጋገጥ ብቻ ነው፡፡
3. አንድ አመራር ከፍ ወዳለ የአመራርነት ቦታ በእድገት ሊመደብ የሚችለው በተሰማራበት ስራ ውጤታማ መሆኑ በምዘና ሲረጋገጥና ለቦታው የተቀመጠውን መስፈርት የሚያሟላ ከሆነ ብቻ ነው፡፡
4. በየትኛውም ደረጃ የሚካሄድ የአመራር ምደባ ምደባ እራስን በራስ የማስተዳደር መብትን በጠበቀ መልኩ በየደረጃው ያለውን ብዝሃነት ባገናዘበ መልኩ ሚዛናዊ ውክልናን የሚያረጋግጥ ሊሆን ይገባል፡፡

5. አባል ያልሆኑ ምሁራንና ከፍተኛ ባለሙያዎችን እና የተፎካካሪ ፓርቲ አባላትን ለመመደብ በሚፈለግበት ጊዜ ከፓርቲው ፕሮግራም የተቀዱ የመንግስት ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች በብቃት የሚያስፈጽሙ መሆናቸው መረጋገጥ አለበት፡፡
6. ፓርቲውን የሚያጠናክር አቅምና ችሎታ ያላቸው ምሁራን፣ ወጣቶችና ሴቶችን ወደ አመራርነት እንዲመጡ የሚያስችል የምደባ ሥርዓት መከተል ያስፈልጋል፡፡
7. የተለየ ሙያና ልምድ የሚሹ የአመራር መደቦች ላይ አግባብነት ያለው ሙያዊ ብቃትና ልምድ ያላቸው እጩ አመራሮች ተለይተው እንዲመደቡ መደረግ አለበት፡፡
8. ለአመራር ምደባ የሚደረገው የእጩ ምልመላና የምደባ ስራ በዚህ መመሪያ የተቀመጡ መርሆዎች፣ መስፈርቶችና ሂደቶች በተከተለ መልኩ መሆን ይኖርበታል፡፡ ከዚህ ውጭ ግልጽነት ለጎደለው፣ መርሆና አሰራርን ያልተከተለ እና መስፈርቱን በማያሟላ አኳኋን ለሚደረግ የአመራር ምደባ መዳቢው አካል ተጠያቂ ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 5

## የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ ከፌደራል እስከ ቀበሌ በፓርቲና በመንግስት በሚደረጉ የአመራር ሹመቶች ወይም ምደባዎች በአመራርነት በሚመደቡ ወይም በሚሾሙ አካላት ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

# ክፍል ሁለት

# የአመራር መደቦች

## አንቀጽ 6

## የአመራር መደቦች ዝርዝር

ለዚህ መመሪያ አፈፃፀም እንዲረዳ ሲባል የአመራር ምደባ የሚካሄድባቸው የአመራር መደቦች ምድብ አንድ፣ ምድብ ሁለት፣ ምድብ ሦስት፣ ምድብ አራት፣ ምድብ አምስትና ምድብ ስድስት በሚል ተከፍሏል፡፡

## አንቀጽ 7

## የምድብ አንድ የአመራር መደቦች

የምድብ አንድ የአመራር መደቦች የሀገሪቱ ፕሬዚዳንት፣ ጠቅላይ ሚኒስትር፣ ም/ጠቅላይ ሚኒስትር፣ የብልጽግና ፓርቲ ዋና ጽ/ቤት ኃላፊ እና የህዝብ ተወካዮችና የፌደሬሽን ምክር ቤቶች ዋና አፈ-ጉባኤዎችና ምክትሎቻቸው የአመራርነት መደቦች ናቸው፡፡

## አንቀጽ 8

## የምድብ ሁለት የአመራር መደቦች

የምድብ ሁለት የአመራር መደቦች የክልል ፕሬዚዳንቶች፣ ሚኒስትሮች፣ ምክትል ፕሬዚዳንቶች፣ ሚኒስቴር ዴኤታዎች፣ የክልል ፓርቲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ሃላፊዎች፣ የክልል አስተባባሪ ኮሚቴዎች፣ የክልል ምክር ቤት አፈ-ጉባኤዎችና ምክትሎቻቸው እና የክልል የብሔረሰቦች ምክር ቤቶች አፈጉባኤዎችና ምክትሎቻቸው እና ከላይ በተጠቀሱ የአመራር መደቦች ማዕረግ ወይም ደረጃ የሚገኙ የአመራርነት መደቦች ናቸው፡፡

## አንቀጽ 9

## የምድብ ሦስት የአመራር መደቦች

የምድብ ሦስት የአመራር መደቦች አስተባባሪ ውስጥ የሌሉ ክልል የፓርቲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የዘርፍ አመራሮች፣ የክልል ካቢኔ አባላት፣ የዞን አስተዳዳሪ፣ የዞን የፓርቲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ሃላፊዎች፣ የዞን አስተባባሪ ኮሚቴ አባላት፣ የፌደራል ተቋም ዋናና ምክትል ዳይሬክተሮች፣ ኮሚሽነሮችና ምክትል ኮሚሽነሮች፣ የባለስልጣን ዋናና ምክትሎቻቸው፣ የዞን ምክር ቤቶች አፈ-ጉባኤዎችና ምክትሎቻቸው፣ የፓርቲ ዋና ጽ/ቤት ሃላፊዎች እና ከላይ በተጠቀሱ የአመራር መደቦች ማዕረግ ወይም ደረጃ የሚገኙ የአመራርነት መደቦች ናቸው፡፡

## አንቀጽ 10

## የምድብ አራት የአመራር መደቦች

የምድብ አራት የአመራር መደቦች አስተባባሪ ውስጥ የሌሉ የዞን የፓርቲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ዘርፍ አመራሮች፣ በክልል የፓርቲ ቅርንጫፍ ምክትል ዘርፍ ሃላፊዎች፣ የክልል ም/ቢሮ ሃላፊዎች፣ የክልል ዋናና ምክትል ዳይሬክተሮች፣ ኮሚሽነሮችና ምክትል ኮሚሽነሮች፣ ዋናና ምክትል ባለስልጣኖች፣ የወረዳ ዋና አስተዳዳሪና በወረዳ ደረጃ ያሉ ከተሞች አስተባበሪ

ኮሚቴዎች እና የወረዳ/በወረዳ ደረጃ ያሉ ከተሞች አፈጉባኤዎችና ምክትሎቻቸው እና ከላይ በተጠቀሱ የአመራር መደቦች ማዕረግ ወይም ደረጃ የሚገኙ የአመራርነት መደቦች ናቸው፡፡

## አንቀጽ 11

## የምድብ አምስት የአመራር መደቦች

የምድብ አምስት የአመራር መደቦች የወረዳ/በወረዳ ደረጃ ያሉ ከተሞች ካቢኔና ምክትል ሃላፊዎች፣ ለወረዳ ተጠሪ የሆኑ ታዳጊ ከተሞች የአመራር መደቦች፣ የከተማ ቀበሌ የአመራር መደቦች እና ከላይ በተጠቀሱ የአመራር መደቦች ማዕረግ ወይም ደረጃ የሚገኙ የአመራርነት መደቦች ናቸው፡፡

## አንቀጽ 12

## የምድብ ስድስት የአመራር መደቦች

የምድብ ስድስት የአመራር መደቦች የገጠር ቀበሌ አመራር መደቦች የአመራርነት መደቦች ናቸው፡፡

# ክፍል ሦስት

# የአመራር ምደባ ሥርዓት

## አንቀጽ 13

## የፌደራል አመራር አመዳደብ ሥርዓት

የፌደራል አመራር አመዳደብ ከዚህ በታች የተመለከተውን ሥርዓት ተከትሎ ይፈፀማል፡፡

1. የፓርቲው ፕሬዝዳንት የሚያስቀምጠውን አቅጣጫ ተከትሎ የፓርቲ ዋና ጽ/ቤት ከክልሎችና ከፌዴራል አደረጃጀት የአመራር ቋት በፌዴራል ተቋማት ሊመደቡ የሚችሉ አመራሮችን በመለየት ፕሮፋይላቸውን አዘጋጅቶ ለፓርቲው ፕሬዚዳንት ያቀርባል፡፡
2. ፓርቲው ገዥ ፓርቲ የሆነ እንደሆነ የፓርቲው ፕሬዝዳንት ጠቅላይ ሚኒስትር ሆኖ እንዲሰየም ለኢ.ፌዲሪ የሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት ይቀርባል፡፡
3. ፕሬዝዳንቱ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባል ያልሆነ እንደሆነ ፕሬዝዳንቱና ምክትል ፕሬዝዳንቶቹ በጋራ ሆነው ለጠቅላይ ሚኒስትር የአመራር መደብ ሦስት የሕዝብ

ተወካዮች ምክር ቤት አባል የሆኑ እጩዎችን በመለየት ለሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ኮሚቴ በማቅረብ ከመካከላቸው አንዱን ያስመርጣል፡፡

4. ፓርቲው ገዥ ፓርቲ የሆነ እንደሆነ ከምክትል ፕሬዝዳንቶች አንዱ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ሆኖ ይመደባል፡፡
5. ከምክትል ፕሬዝደንቶች አንዱ የፓርቲ ዋና ጽ/ቤት ኃላፊ ሆኖ ይመደባል፡፡
6. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2-5 የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ ፓርቲው ገዥ ፓርቲ በሚሆንበት ወቅት የፓርቲው ፕሬዝዳንት ከምክትል ፕሬዚዳንቶች ጋር በመነጋገር እጩ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ፕሬዝዳንት፣ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈጉባኤና ምክትል አፈጉባኤ፣ የፌዴሬሽን ምክር ቤት አፈ-ጉባኤ እና ምክትል አፈጉባኤውን፣ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩን እና የፓርቲ ዋና ጽ/ቤት ኃላፊን ከመግለጫ ጋር ለሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴው ያቀርባል፡፡
7. የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 6 መሠረት የቀረቡለትን እጩ አመራሮች ሹመት መርምሮ ያጸድቃል፡፡
8. በሚኒስትርና በሚኒስትር ማዕረግ የሚመደቡ አመራሮች፣ የሚኒስትር ዴኤታዎችና በሚኒስትር ዴኤታ ማዕረግ የሚመደቡ አመራሮች፣ የባለስልጣን ዋናና ምክትሎቻቸው እና የኤጀንሲ ዋናና ምክትል ዳይሬክተሮች፣ ኮሚሽነሮችና ምክትል ኮሚሽነሮችን ሹመት የፓርቲው ፕሬዚዳንት ከምክትል ፕሬዚዳንቶች ጋር በመነጋገር ይወስናል፡፡
9. በፌዴራል ደረጃ የሚከናወን የአመራር ምደባ የብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የህዝብ ብዛትን ከግምት በማስገባት ሚዛናዊ ውክልና በሚያረጋግጥ መልኩ መከናወን ይኖርበታል፡፡
10. በአንድ የፌዴራል ተቋም ውስጥ የሚከናወን ምደባ ህብረ-ብሄራዊ ስብጥርን በጠበቀ መልኩ መከናወን ይኖርበታል፡፡
11. በዚህ አንቀጽ ከፍ ብሎ በንዑስ አንቀጽ 1-10 የተጠቀሱት እንደተጠበቁ ሆነው የፓርቲ አባላት ያልሆኑ እጩ አመራሮች መመደብ ሲያስፈልግ ከአመራር ጥል ውጭ በዚህ መመሪያ በተደነገገው መሰረት ምደባው ሊከናወን ይችላል፡፡

## አንቀጽ 14

## የክልል አመራር አመዳደብ ሥርዓት

የክልል አመራር አመዳደብ ከዚህ በታች የተመለከተውን ሥርዓት ተከትሎ ይፈፀማል፡፡

1. ለመንግስትም ሆነ ለፓርቲ ሥራ በየክልሎቹ የሚመደቡ የፓርቲ አስተባባሪ ኮሚቴ እጩ አባላት በክልሉ አስተባባሪ ኮሚቴ አማካኝነት ተመልምለው ዝርዝር ፕሮፋይላቸው ለፓርቲው ዋና ጽ/ቤት ይቀርባል፣
2. የቀረበው ዝርዝር በፓርቲው ፕሬዚዳንትና በዋና ጽህፈት ቤት ኃላፊ ከታየ በኋላ በፌደራልና ክልል ፓርቲ አመራሮች የጋራ መድረክ ቀርቦ የሚጸድቅ ይሆናል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ የፌደራልና የክልል ፓርቲ አመራሮች የጋራ መድረክ ስብሰባ ተካሂዶ እስከሚፀድቅ ድረስ ክፍተት እንዳይፈጠር የተጓደሉ የክልል አስተባባሪ ኮሚቴ አባላትን የፓርቲው ፕሬዚዳንትና የፓርቲ ዋና ጽ/ቤት ኃላፊ በጋራ በመሆን የሚሞሉ ይሆናል፡፡
4. የክልል ካቢኔ አባላትን ጨምሮ በክልል ደረጃ በሚገኙ የአመራር ቦታዎች የአመራር ምደባ በክልሉ አስተባባሪ ኮሚቴ የሚከናወን ይሆናል፡፡
5. የክልል ካቢኔ አባላትን ጨምሮ በክልል ደረጃ በሚገኙ የአመራር ቦታዎች ላይ የፓርቲ አባላት የሚመደቡ ሲሆን በክልሉ ፓርቲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት አመራር ኮሚቴ ከተደራጀው የአመራር ፑል ውስጥ በማወዳደር ይሆናል፡፡
6. በክልል ደረጃ የሚከናወን የአመራር ምደባ በክልሉ ያለውን ብዝሃነት ከግምት በማስገባት ሚዛናዊ ውክልና በሚያረጋግጥ መልኩ መከናወን ይኖርበታል፡፡
7. በዚህ አንቀጽ ከፍ ብሎ በንዑስ አንቀጽ 1-6 የተጠቀሱት እንደተጠበቁ ሆነው የፓርቲ አባላት ያልሆኑ እጩ አመራሮች መመደብ ሲያስፈልግ ከአመራር ፑል ውጭ በዚህ መመሪያ በተደነገገው መሰረት ምደባው ሊከናወን ይችላል፡፡

## አንቀጽ 15

## የዞን አመራር አመዳደብ ሥርዓት

የዞንና በዞን ደረጃ ያሉ ከተሞች የአመራር አመዳደብ ከዚህ በታች የተመለከተውን ሥርዓት ተከትሎ ይፈፀማል፡፡

1. የዞን አስተባባሪ ኮሚቴ፣ ካቢኔ አባላት፣ አፈ-ጉበኤዎች እና በተመሳሳይ ደረጃ ያለ ምደባ በራሳቸው የፓርቲ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት አመራር ኮሚቴ ከተደራጀው የአመራር ፑል ውስጥ በአስተባባሪ ኮሚቴያቸው ታይቶ ለክልል አስተባባሪ ኮሚቴ ይቀርባል፡፡
2. የክልሉ አስተባባሪ ኮሚቴ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የቀረበለትን ዝርዝር መርምሮ ያፀድቃል፡፡
3. የዞን ምክትል ኃላፊዎች እና የሌሎች የዞን አመራሮች ምደባ በቅርንጫፍ ጽ/ቤታቸው አመራር ኮሚቴ ከሚዘጋጅ የአመራር ፑል ውስጥ በአስተባባሪ ኮሚቴያቸው ታይቶ ምደባ ይከናወናል፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ከፍ ብሎ በንዑስ አንቀጽ 1-3 የተጠቀሱት እንደተጠበቁ ሆነው የፓርቲ አባላት ያልሆኑ እጩ አመራሮች መመደብ ሲያስፈልግ ከአመራር ፑል ውጭ በዚህ መመሪያ በተደነገገው መሰረት ምደባው ሊከናወን ይችላል፡፡

## አንቀጽ 16

## የወረዳ አመራር አመዳደብ ሥርዓት

የወረዳና በወረዳ ደረጃ ያሉ ከተሞች አመራር አመዳደብ ከዚህ በታች የተመለከተውን ሥርዓት ተከትሎ ይፈጽማል፡፡

1. በወረዳና በወረዳ ደረጃ የሚታዩ ከተሞች አስተባባሪ ኮሚቴ አባላት፣ የካቢኔ አባላት፣ አፈ-ጉበኤዎች እና በተመሳሳይ ደረጃ ያሉ የሌሎች አመራሮች ምደባ በራሳቸው የፓርቲ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት አመራር ኮሚቴ ከሚዘጋጅ የአመራር ፑል ውስጥ በአስተባባሪ ኮሚቴያቸው ታይቶ ለክልል ወይም ለዞን ወይም ለክፍለ ከተማ አስተባባሪ ኮሚቴ ይቀርባል፡፡
2. የክልል ወይም የዞን ወይም የክፍለ ከተማ አስተባባሪ ኮሚቴ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የቀረበለትን ዝርዝር መርምሮ ያፀድቃል፡፡
3. የወረዳና በወረዳ ደረጃ የሚታዩ ከተሞች ምክትል ኃላፊዎች እና የሌሎች አመራሮች ምደባ በራሳቸው የፓርቲ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት አመራር ኮሚቴ ከሚዘጋጅ የአመራር ፑል ውስጥ በአስተባባሪ ኮሚቴያቸው ታይቶ የሚፀድቅ ይሆናል፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ከፍ ብሎ በንዑስ አንቀጽ 1-3 የተጠቀሱት እንደተጠበቁ ሆነው የፓርቲ አባላት ያልሆኑ እጩ አመራሮች መመደብ ሲያስፈልግ ከአመራር ፑል ውጭ በዚህ መመሪያ በተደነገገው መሰረት ምደባው ሊከናወን ይችላል፡፡

## አንቀጽ 17

## ለወረዳ ተጠሪ የሆኑ ታዳጊ ከተሞች አመራር ምደባ

ለወረዳ ተጠሪ የሆነ ታዳጊ ከተሞች አመራር አመዳደብ ከዚህ በታች የተመለከተውን ሥርዓት ተከትሎ ይፈፀማል፡፡

1. ለወረዳ ተጠሪ የሆኑ ታዳጊ ከተሞች አመራር ምደባ በወረዳ ፓርቲ አመራር ኮሚቴ ከተደራጀው የአመራር ፑል እጩዎች ተለይተው ለወረዳ አስተባባሪ ኮሚቴ ይቀርባል፡፡
2. የወረዳው አስተባባሪ ኮሚቴ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የቀረበለትን ዝርዝር መርምሮ ያፀድቃል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ከፍ ብሎ በንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 የተጠቀሱት እንደተጠበቁ ሆነው የፓርቲ አባላት ያልሆኑ እጩ አመራሮች መመደብ ሲያስፈልግ ከአመራር ፑል ውጭ በዚህ መመሪያ በተደነገገው መሰረት ምደባው ሊከናወን ይችላል፡፡

## አንቀጽ 18

## የቀበሌ አመራር አመዳደብ ሥርዓት

የቀበሌ አመራር አመዳደብ ከዚህ በታች የተመለከተውን ሥርዓት ተከትሎ ይፈፀማል፤

1. በቀበሌ ደረጃ የሚከናወን የአመራር ምደባ በወረዳ የፓርቲ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት አመራር ኮሚቴ ከሚዘጋጅ የአመራር ፑል ውስጥ እጩዎች ተለይተው ወረዳው አስተባባሪ ኮሚቴ ይቀርባሉ፡፡
2. የወረዳው አስተባባሪ ኮሚቴ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የቀረበለትን ዝርዝር መርምሮ ያፀድቃል፡፡

## አንቀጽ 19

## በውድድር ስለሚያዙ የአመራር መደቦች

1. በዚህ መመሪያ የተደነገጉ የአመራር የአመዳደብ ስርዓትን ተከትሎ የሚፈፀም የአመራር ምደባ እንደተጠበቀ ሆኖ የልማት ድርጅቶችና የተለየ እውቀትና ልምድ የሚጠይቁ የአመራር መደቦች ተፈላጊ መስፈርቶችን በሚያሟሉ አመልካች እጩዎች መካከል በሚደረግ ውድድር ሊያዙ ይችላሉ፡፡
2. በየደረጃው በሚገኙ የአመራር መደቦች ላይ አመራር ለመመደብ ስልጣን የተሰጠው አካል፡-

ሀ) በውድድር መያዝ ያለባቸውን መደቦች በየግዜው እያጠና/እየመረመረ የሚወስን ይሆናል፡፡

ለ) በውድድሩ መሳተፍ የሚችሉ አካላትን፣ የውድድር መስፈርቶችን እና የውድድር ሂደቱን በተመለከተ በግልጽ አቅጣጫ ያስቀምጣል::

ሐ) በተቀመጠው አቅጣጫ መሰረት ውድድሩን የሚመሩና የሚያስፈጽሙ አካላትን በመሰየም ውድድሮቹ እንዲከናወኑ ያደርጋል፡፡

መ) የውድድር ሂደቱን በመገምገም የአሸናፊዎችን ውጤት መርምሮ ያፀድቃል፡፡

ሠ) በጸደቀው ውጤት መሰረት የአመራር ስምሪቱ ተግባራዊ እንዲሆን ያደርጋል፡፡

3. በውድድር መያዝ ስላለባቸው የአመራር መደቦች በተመለከተ ከላይ ከተዘረዘሩት ድንጋጌዎች በተጨማሪ የፓርቲው ዋና ጽህፈት ቤት ዝርዝር የአሰራር ስርዓት በመዘርጋት በየደረጃው እንዲተገበር ሊያደርግ ይችላል፡፡

## <u>አንቀጽ 20</u>

## የብልጽግና ፓርቲ አባል ያልሆነ አመራር ምደባን በተመለከተ

1. በአመራር ቋት ውስጥ ከተያዙት መካከል ለአመራር መደቡ ብቁ የሆኑ የብልጽግና አባላት ማግኘት ካልተቻለ በየደረጃው የምደባ ስልጣን የተሰጣቸው አካላት በሙያቸው ከፍተኛ አስተዋጽኦ ማበርከት የሚችሉ አባል ያልሆኑ ምሁራንና ከፍተኛ ባለሙያዎችን በመለየት መመደብ ይችላሉ፡፡
2. የአገራችንን የፖለቲካ ሥርዓት ለማዘመንና በትብብር የመስራት ባህልን ለማሳደግ ሲባል በተለያዩ የአመራርነት መደቦች በዚህ መመሪያ የተቀመጡ መስፈርቶችን የሚያሟሉ የተፎካካሪ ፓርቲ አባላትን በየደረጃው የምደባ ስልጣን የተሰጣቸው አካላት መመደብ ይችላሉ፡፡
3. የብልጽግና አባላት ያልሆኑ ምሁራንና ከፍተኛ ባለሙያዎችን እንዲሁም የተፎካካሪ ፓርቲ አባላትን ለመመደብ በሚፈለግበት ጊዜ ከፓርቲው ፕሮግራም የተቀዱ የመንግስት ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች በብቃት የሚያስፈጽሙ መሆናቸውን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡

## አንቀጽ 21

## ለአመራር ምደባ እጩዎችን ስለማቅረብ

1. በማንኛውም ደረጃ ለሚደረግ የብልጽግና ፓርቲ አባላት የአመራር ምደባ ለአንድ መደብ በእኩል ደረጃ የሚታዩ ሦስት እጩ አመራሮች ከአመራር ቋት /ፑል/ ውስጥ ይቀርባሉ፡፡
2. የብልጽግና አባላት ያልሆኑ ምሁራንና ከፍተኛ ባለሙያዎችን እና የተፎካካሪ ፓርቲ አባላትን ለመመደብ በሚፈለግበት ጊዜ የቁጥር ገደብ ሳይኖር በእኩል ደረጃ የሚታዩ እጩ አመራሮች ተለይተው ከሌሎች የተሻለው ይወሰዳል፡፡

## አንቀጽ 22

## ከሌላ መዋቅር አመራር መመደብን ወይም ማዘዋወርን በተመለከተ

1. የምደባ ሥልጣን የተሰጠው አካል አንድን እጩ አመራር ከሌላ መዋቅር መውሰድ ሲያስፈልግ በቅድሚያ ይሰራበት ከነበረበት መዋቅር ሙሉ ፕሮፋይሉ ተወስዶ መስፈርቱን የሚያሟላ ስለመሆኑ ይረጋገጣል፡፡
2. የፌዴራል ወይም የሌላ ክልል አመራር የሆነ አባል መመደብ የሚቻለው የፓርቲው ዋና ጽ/ቤት ሲፈቅድ ወይም የሚሰራበት ክልል ፍቃደኝነቱን በጽሑፍ ሲያሳውቅ ብቻ ይሆናል፡፡
3. ከአንድ መዋቅር ወደ ሌላ መዋቅር የሚደረግ የአመራር ምደባ አንድ ደረጃ ከፍ ባለው አስተባባሪ ኮሚቴ ታይቶ መጽደቅ ይኖርበታል፡፡

# ክፍል አራት

# የአመራር ምደባ መስፈርቶች

## አንቀጽ 23

## የግል ባህሪ /ስብዕና/

1. በማንኛውም የአመራርነት መደብ የሚመደብ አባል የሚከተሉትን የግል ባህሪ (ስብዕና) መስፈርቶች ሊያሟላ ይገባል፡፡

   ሀ) ጤናማ አመላካከትና የፖለቲካ እምነት /ቅንነትና አቋም/ ያለው፣

ለ) ስልጣን ላይ የተስተካከለ እይታ ያለው /ስልጣን ለህዝብ መገልገያ መሆኑን አምኖ የተቀበለና ለተግባራዊነቱ የሚተጋ/ ፣

ሐ) በተሰማራበት የሥራ መስክ ዘወትር ስራውን በከፍተኛ ትጋትና የኃላፊነት ስሜት የሚፈጽም እና ፓርቲው የሚሰጠውን ፓርቲውንና ህዝቡን የማገልገል ሃላፊነት ተቀብሎ በተነሳሽነት፣ በቁርጠኝነትና በታማኝነት ሊወጣ የሚችል መሆኑ፣

መ) ግብረገባዊ ስነ-ምግባርን የተላበሰ፣ በህዝብ ዘንድ ተቀባይነት ከሌላቸው ተግባራት የራቀ እና ለሌሎች አርአያ የሆነ፣

ሠ) የማህበረሰቡን የሞራል እሴቶች በሚገባ የሚጠብቅና የሚያስጠብቅ፣

ረ) ዲሞክራሲያዊ ባህሪን የተላበሰና ማንኛውንም አሉታዊ ወይም አዎንታዊ ሃሳብ በዲሞክራሲያዊ መንገድ የማስተናገድ ባህል ያለው፣

ሰ) በሂደት በሥራው እና በአጠቃላይ እንደ ፓርቲና እንደ ሀገር የሚያጋጥሙትን ተግዳሮቶችንና ፈተናዎችን ተቋቁሞ ለመስራት ዝግጁ የሆነና ፈተናዎችን ወደ እድል መቀየር የሚችል፣

ሸ) መርህን፣ ህግንና ተቋማዊ አሰራርን የሚያከብርና የሚያስከብር፤

ቀ) ጤናማ ማህበራዊ ግንኙነት ያለው፣ ከሥራ ባልደረቦች ጋር በትብብር የመስራት ስብዕና ያለው እና አብረውት በሚሰሩ ሰዎች ላይ አዎንታዊ ተጽእኖ ማሳደር የሚችል ስብእና ያለው እና

በ) የፓርቲውን መተዳደሪያ ደንብ አክብሮ ግዴታዎችን በአግባቡ የሚወጣ አመራር መሆን ይኖርበታል፡፡

## አንቀጽ 24

## የፖለቲካ ብቃት

1. ማንኛውም በአመራርነት መደብ የሚመደብ አባል በየደረጃው በመዳቢው አካል የፖለቲካ ብቃቱ የሚመዘነው በሚከተሉት መስፈርቶች ላይ በመመስረት ይሆናል፡፡

 ሀ) በፓርቲው ፕሮግራም፣ መተዳደሪያ ደንብ፣ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች የተሟላ ግንዛቤና እምነት ያለው፣

 ለ) በእጩነት ለቀረበበት መደብ በሚመጥን መልኩ ወቅታዊ አከባቢያዊ፣ አገራዊ፣ ቀጠናዊ፣ አህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ እና

ርዕዮተ ዓለማዊ ሁኔታ በሚገባ በመተንተንና በመመርመር እድሎችንና ተግዳሮቶችን ለይቶ መፍታት የሚችል ብቃት ያለው፣

ሐ) ከፓርቲው ፕሮግራም በሚመነጩ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ፖሊሲና ስትራቴጂዎች ላይ በእጩነት ለቀረበበት መደብ በሚመጥን መልኩ ግንዛቤ ኖሮት የህዝቡን ተሳትፎና ድጋፍ እንደ አቅም መጠቀም የሚያስችሉ ውጤታማ ስልቶችን ቀይሶ አመራር የመስጠት ብቃት ያለው፣

መ) ባለበት ቦታ ቀጣይነት ያለው የውስጠ ፓርቲ አንድነትና ጥንካሬን ለማጎልበት የሚያስችሉ ስልቶችን እየቀየሰ የፓርቲ ግንባታ ስራዎችን በውጤታማነት የመምራት የፖለቲካ ብቃት ያለው፣

ሠ) የፖለቲካ ባህል እንዲዳብር የተፎካካሪ ፓርቲዎችን ጨምሮ ሁሉም ባለ ድርሻ አካላት የበኩላቸውን አውንታዊ ሚና እንዲጫወቱ የፖለቲካ ብቃትና ቁርጠኝነት ያለው፣

ረ) ሀገራዊ፣ ክልላዊና አከባቢያዊ የፓርቲና የመንግስት መደበኛ ስራዎች በተቀናጀ፣ በተጣጣመ፣ ሚዛን በጠበቀና ውጤታማ በሆነ አግባብ እንዲፈፀሙ የፖለቲካ አቅጣጫዎችንና ስልቶችን ቀይሶ የመምራት ብቃት ያለው፣

ሰ) የኢትዮጵያውያን ሕብረ-ብሔራዊ ወንድማማችነት እና እህትማማችነት እንዲጎለብት አጥብቆ የሚሰራ፣ አገራዊ አንድነትን ለማጠናከር የሚተጋ እና ዋልታ ረገጥ አስተሳሰቦች በመታገልና በማታገል ረገድ የመሪነት ሚና የሚጫወት፣

ሸ) የተሰጠውን ተልዕኮ በብቃት ሊመራ የሚችል የፖለቲካ ብቃት ያለውና በየጊዜው እራስን በማብቃት ሌላውን የማብቃት ችሎታ የተሻለ የሆነ፣

ቀ) በአመራርነት እየሰሩ ላሉ አመራሮች የፖለቲካ ብቃት ደረጃቸው በፓርቲው የምዘና መመሪያ መሰረት ከተካሄደው የአመራሩ የፓርቲ ሥራዎች አፈፃፀም ምዘና ውጤት ጋር በቀጥታ እንዲያያዝ ይደረጋል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተዘረዘሩት መስፈርቶች ከታች ወደ ላይ ከምድብ ስድስት ወደ ምድብ አንድ መስፈርቶች እየጠነከሩ የሚሄዱ ሲሆን የእጩዎች የፖለቲካ ብቃት ደረጃ በጥልቀት በዚህ መመሪያ በየደረጃው የምደባ ኃላፊነት በተሰጣቸው አካላት የሚታይ ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 25

## የአመራር ብቃት

1. ማንኛውም በአመራርነት መደብ የሚመደብ አባል በየደረጃው በመዳቢው አካል የአመራር ብቃቱ የሚመዘነው በሚከተሉት መስፈርቶች ላይ በመመስረት ይሆናል፡፡
   ሀ) ተቋማዊ የአሰራር ሥርዓት በመዘርጋት ከፍተኛ የመሪነት ሚናን መወጣት የሚችል፤
   ለ) በሚመደብበት የአመራር እርከን የዜጎችን ፍትሃዊ ተጠቃሚነት፤ ሁለንተናዊ ነፃነትና እኩልነትን ለማረጋገጥ የሚያስችል እቅዶችን ነድፎ የተሟላ አመራር ለመስጠት የሚችል፣
   ሐ) ከፓርቲው ፕሮግራም በመነሳት ብሔራዊ የፖሊሲና የስትራቴጂ ሃሳቦችን ወደ ተግባር ለመቀየር የሚያስችሉ ስልቶችን ነድፎ አመራር መስጠትና የማስፈጸም አቅም ያለው፣
   መ) ከሚወስደው የአመራርነት ኃላፊነት አኳያ ውስብስብና ተለዋዋጭ የሆነውን አከባቢያዊ፣ አገራዊ፣ ቀጠናዊ፣ አህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ ሁኔታዎችን በሚገባ ተንትኖ በአግባቡ አመራር እየሰጠ በሚገባ ማስፈጸም የሚችል፣
   ሠ) ባለራዕዮችንና ተተኪዎችን ለመገንባትና ለማብዛት አቅዶ መስራት የሚችል፤ በሂደቱም ከፍተኛ ተስጥኦና ክህሎት ያለው፣
   ረ) ሁኔታዎችን አመዛዝኖ የመወሰን ብቃት ያለው እንዲሁም ለወደፊቱ ሊከሰቱ የሚችሉ አደጋዎችንና ፈተናዎችን ቀድሞ በመገመት አማራጭ የመፍትሄ ዘዴዎችን መቀየስ የሚችል፣
   ሰ) በሀገር አቀፍ ደረጃ የተነደፉ ግቦችን በሚፈለገው ደረጃ ለማሳካት በሚደረገው ጥረት በአንድ አካባቢ የተመዘገቡ መልካም ተሞክሮዎችን እንዲቀመሩና ወደ ሌሎች አካባቢዎች እንዲሰፉ አመራር የመስጠት ብቃት ያካበተ፣
   ሸ) ከፍተኛ የኮሙዩኒኬሽን ክህሎት ያለው እና በሚመደብበት የአመራር ደረጃ ውጤታማ የሚዲያ አጠቃቀምን ማከናወን እና ማስተግበር የሚችል፣
   ቀ) ከሌሎች ጋር በመተባበር፣ በመደጋገፍ፣ በመግባባት እና በፉክክርና ትብብር ሚዛን ጠብቆ መሥራት የሚችል፣ የትኛውንም አሉታዊ ተጽዕኖ መቋቋም የሚችል፣ በቡድን ሥራ የሚያምን እና አመራር ለመስጠት ብቃት ያለው ሊሆን ይገባል፡፡

በ) በአመራርነት እየሰሩ ላሉ አመራሮች የአመራር ብቃት ደረጃቸው በፓርቲው የምዘና መመሪያ መሰረት ከተካሄደው የአመራሩ የሥራ አፈፃፀም ምዘና ውጤት ጋር በቀጥታ እንዲያያዝ ይደረጋል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተዘረዘሩት መስፈርቶች ከታች ወደ ላይ ከምድብ ስድስት ወደ ምድብ አንድ መስፈርቶች እየጠነከሩ የሚሄዱ ሲሆን የእጩዎች የፖለቲካ ብቃት ደረጃ በጥልቀት በዚህ መመሪያ በየደረጃው የምደባ ኃላፊነት በተሰጣቸው አካላት የሚታይ ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 26

## የትምህርት ዝግጅት

1. የአመራርነት ቦታው ባለው ባህሪ የተለየ የሙያ ዘርፍ የማይሻ ከሆነ ማንኛውም በምድብ አንድ፣ ሁለትና ሦስት የአመራርነት መደብ የሚመደብ አባል በየትኛውም የትምህርት መስክ ቢያንስ የሁለተኛ ዲግሪ የትምህርት ደረጃ ያለው መሆን ይኖርበታል፡፡
2. የአመራርነት ቦታው ባለው ባህሪ የተለየ የሙያ ዘርፍ የሚሻ ከሆነ ማንኛውም በምድብ አንድ፣ ሁለትና ሦስት የአመራርነት መደብ የሚመደብ አባል ከቦታው ጋር ግንኙነት ባላቸው የሙያ ዘርፎች የትምህርት መስኮች ቢያንስ ሁለተኛ ዲግሪ ያለው ሊሆን ይገባል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ የያታና ሌሎች ብዝሃነትን ለማስተናገድ ሲባል የመፈጸም ብቃት ያለው መሆኑ የምደባ ስልጣን በተሰጠው አካል ከታመነበት በልዩ በሁኔታ የመጀመሪያ ዲግሪ ያለው ሊሆን ይችላል፡፡
4. ማንኛውም በምድብ አራትና አምስት የአመራርነት መደብ የሚመደብ አባል በየትኛውም የትምህርት መስክ ቢያንስ የመጀመሪያ ዲግሪ የትምህርት ደረጃ ያለው ሊሆን ይገባል፡፡
5. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 4 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ የመምራት ብቃትን ከግምት ውስጥ በማስገባት እንዲሁም የትምህርት ተደራሽነት ችግር ባለበት ሁኔታ እና የያታና ሌሎች ብዝሃነትን ለማስተናገድ ሲባል የምደባ ስልጣን በተሰጠው አካል ከታመነበት በልዩ ሁኔታ ዲፕሎማ/ተማጣጣኝ የትምህርት ደረጃ ያለው አመራር ሊመደብ ይችላል፡፡
6. ማንኛውም በምድብ ስድስት የአመራርነት መደብ የሚመደብ አባል በየትኛውም የትምህርት መስክ ቢያንስ ዲፕሎማ/ተማጣጣኝ የትምህርት ደረጃ ያለው ሊሆን ይገባል፡፡

7. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 6 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ በአርብቶ አደርና ትምህርት ተደራሽነት ችግር ባለባቸው አከባቢዎች ማንበብና መጻፍ የሚችል ሊመደብ ይችላል፡፡

## አንቀጽ 27

## የሥራ ልምድ

1. ማንኛውም በምድብ አንድና ሁለት የአመራርነት መደብ የሚመደብ አባል በተለያዩ የአመራር እርከኖች በአመራርነት ቢያንስ ለ10 ዓመት ያገለገለ እና የካበተ ዘርፈ ብዙ የሥራ ልምድ ያለው ሊሆን ይገባል፡፡
2. ማንኛውም በምድብ ሦስት የአመራርነት መደብ የሚመደብ አባል ከሌላው የሥራ ልምዱ በተጨማሪ በተለያዩ የአመራር እርከኖች በአመራርነት ቢያንስ ለ5 ዓመት ያገለገለ ሊሆን ይገባል፡፡
3. ማንኛውም በምድብ አራት የአመራርነት መደብ የሚመደብ አባል በተለያዩ የአመራር እርከኖች በአመራርነት ቢያንስ ለ3 ዓመት ያገለገለ ሊሆን ይገባል፡፡
4. ማንኛውም በምድብ አምስት የአመራርነት መደብ የሚመደብ አባል በተለያዩ የሥራ መስኮች ቢያንስ የ2 ዓመት የሥራ ልምድ ያለው ሊሆን ይገባል፡፡
5. ማንኛውም በምድብ ስድስት የአመራርነት መደብ የሚመደብ አባል በመሰረታዊ ድርጅት፣ ህዋስና የሕዝብ አደረጃጀቶች በአመራርነት ቢያንስ ለ2 ዓመት ያገለገለ ሊሆን ይገባል፡፡
6. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1-5 የተደነገገው እንደተጠበቀው ሆኖ መዳቢው አካል የግለሰቡን ሙያ፣ እውቀትና የመምራት ብቃት በማየት ካመነበት በዚህ አንቀጽ የተመለከተዉን የአመራርነት ልምድ ባይሟላም በልዩ ሁኔታ ሊመደብ ይችላል፡፡

# ክፍል አምስት

# አመራር ከኃላፊነት ስለሚነሳበትና የቅሬታ አቀራረብ ሥርዓት

## አንቀጽ 28

## አመራር ከኃላፊነት የሚነሳባቸው ምክንያቶች

አንድ አመራር ከኃላፊነት ሊነሳ የሚችለው

1. በግል ምክንያት ከኃላፊነቱ ለመነሳት ሲወስን፣
2. በሀሰተኛ መረጃ የማይገባው ምደባ ማግኘቱ ሲረጋገጥ፣
3. የሥነ-ምግባር፣ የሥራ አፈጻጸም እና የአመለካከት ችግር እንዳለበት በፓርቲው የምዘና መመሪያ ወይም የዲሲፕሊን መመሪያ መሰረት ተረጋግጦ ከኃላፊነቱ እንዲነሳ ሲወሰን፣
4. በፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ ወይም በዚህ መመሪያ መሰረት የአገልግሎት ዘመኑን ሲያጠናቅቅ ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 29

## አመራር ከኃላፊነት ስለሚነሳበት ሥርዓት

1. አንድ አመራር በፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ ወይም በዚህ መመሪያ መሰረት የአገልግሎት ዘመኑን ሲያጠናቅቅ ለሌላ ኃላፊነት ካልታጨ በስተቀር የመሾም/የመመደብ ሥልጣን የተሰጠው አካል በክብር የሚያሰናብተው ይሆናል፡፡
2. አንድ አመራር ከኃላፊነት በሚያስነሳ መልኩ የፓርቲውን የሥነ-ምግባር ደንብ የጣሰ እንደሆነ ወይም የአመለካከት ችግር የታየበት እንደሆነ ወይም ከሕዝብ በተደጋጋሚ ቅሬታ የሚቀርብ እንደሆነ የቅርብ ኃላፊው ወይም አመራሩ አባል የሆነበት አደረጃጀት ይህንኑ በመዘርዘርና በማስረጃ በማስደገፍ አመራሩን ለሾመው ወይም ለመደበው አካል ያቀርባል፡፡
3. አንድ አመራር በፓርቲው የምዘና መመሪያ መሰረት አፈጻጸሙ ከተመዘነ በኋላ ውጤቱ ከኃላፊነት የሚያስነሳው እንደሆነ መዛኙ አካል አመራሩን ለሾመው ወይም ለመደበው አካል ዝርዝር ሪፖርት ያቀርባል፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 እና 3 መሠረት ዝርዝር ሪፖርት የቀረበለት አካል የሪፖርቱን ትክክለኛነት ካረጋገጠ አመራሩን ከኃላፊነቱ እንዲነሳ ይወስናል፡፡

5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 መሰረት ከኃላፊነት የማንሳት ውሳኔ እንደተጠበቀ ሆኖ አመራሩ በሕግ የሚያስጠይቅ ጥፋት ፈጽሞ የተገኘ መሆኑን የሾመው ወይም የመደበው አካል ያረጋገጠ እንደሆነ አስፈላጊውን ማስረጃዎች ለሚመለከተው የህግ አካል የማስተላለፍ ኃላፊነት ይኖርበታል፡፡

## <u>አንቀጽ 30</u>

## ውሳኔ ስለማሳወቅ

በዚህ መመሪያ መሠረት አንድ አመራር ከኃላፊነቱ እንዲነሳ ሲወሰን የውሳኔው ቅጅ በጽሁፍ ይሰጠዋል፡፡

## <u>አንቀጽ 31</u>

## ከኃላፊነት የተነሳ አመራር ምደባ

1. ከኃላፊነት የተነሳ አመራር የፈፀመው ጥፋት ከአመራር ቋት ውስጥ የማያስወጣው ሆኖ ሲገኝ በሚመጥነው የአመራር ደረጃ ሊመደብ ይችላል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ የፈፀመው ጥፋት ከአመራር ቋት ውስጥ የማያስወጣው ከኃላፊነት የተነሳ አመራር የሚመጥነው የአመራር መደብ እስከሚገኝ ድረስ መስፈርቱን በሚያሟላው የሲቪል ሰርቪስ መደብ እንዲመደብ ይመቻችለታል፡፡
3. ከኃላፊነቱ የተነሳ አመራር የፈፀመው ጥፋት ከአመራር ቋት ውስጥ የሚያስወጣው የሆነ እንደሆነ መስፈርቱን በሚያሟላው የሲቪል ሰርቪስ መደብ እንዲመደብ ይመቻችለታል፡፡

## <u>አንቀጽ 32</u>

## የቅሬታ አቀራረብ ሥርዓት

1. በአመራር ቋት ውስጥ የተያዘ ሆኖ በክፍት የአመራር መደቦች ላይ ምደባ ሲከናወን በእጩነት ያልተካተተ አባል ቅሬታውን ለሚመለከተው የፓርቲ መዋቅር ሊያቀርብ ይችላል፤

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት አቤቱታ የቀረበለት አካል በፓርቲው የመተዳደሪያ ደንብና አግባብነት ባላቸው መመሪያዎች መሠረት ቅሬታውን ያስተናግዳል፤
3. አቤቱታ የቀረበለት አካል በሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘ ወገን በየደረጃው ለሚገኙ የኢንስፔክሽን እና የሥነ ምግባር ኮሚሽን ቅሬታውን ሊያቀርብ ይችላል፡፡
4. ከአመራርነት እንዲነሳ በተሰጠ ውሳኔ ቅር የተሰኘ አመራር ቅሬታውን በየደረጃው ለሚገኝ የኢንስፔክሽንና ሥነ-ምግባር ኮሚሽን ያቀርባል፡፡ ቅሬታ የቀረበለት የኢንስፔክሽንና የሥነ ምግባር ኮሚሽን አካል የቅሬታ አቅራቢውን አቤቱታ የተቀበለ እንደሆነ ይህንኑ ውሳኔ አመራሩን ላነሳው አካል ያሳውቃል፡፡
5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 መሠረት የኮሚሽኑ ውሳኔ የደረሰው አካል በውሳኔው የተስማማ እንደሆነ አመራሩን ወደቀድሞው መደብ ይመልሰዋል ወይም መደቡ በሌላ ሰው ተይዞ ከሆነ በሌላ ተመሣሣይ ማዕረግ ወይም ደረጃ ላይ ባለው መደብ ላይ ይመድባል፡፡ አመራሩን ያነሳው አካል ኮሚሽኑ በሰጠው ውሳኔ ያልተስማማ እንደሆነ ይህንኑ ውሳኔ ለቅሬታ አቅራቢውና ለኮሚሽኑ ያሳውቃል፡፡
6. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 5 መሠረት በተሰጠው ውሳኔ ያልተስማማ አመራር ውሳኔ ላስተላለፈው የኢንስፔክሽንና ስነምግባር ኮሚሽን መዋቅር የበላይ አካል ለሆነው የፓርቲ መዋቅር በአንድ ሳምንት ጊዜ ውስጥ ይግባኙን ሊያቀርብ ይችላል፡፡

[

# ክፍል ስድስት

# ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## <u>አንቀጽ 33</u>

## የአመራር ቋት

የፓርቲው ዋና ጽ/ቤት እና በየደረጃው የሚገኙ የፓርቲ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቶች በኃላፊነት ላይ ካሉ አመራሮች በተጨማሪ ከፓርቲ አባላት መካከል በብልጽግና እሳቤዎች ዙሪያ ባላቸው ግንዛቤ፣ የብልጽግናን ራዕይ እውን ለማድረግ ባላቸው ቁርጠኝነት፣ በብቃታቸው፣ በአስተሳሰብ ጥራታቸውና በባህሪያቸው የተሻሉትን አባላት በመለየት የአመራሮች ቋት ያደራጃሉ፡፡

## አንቀጽ 34

## የሴቶችና የወጣቶች ውክልና

1. በየደረጃው የሚገኙ የፓርቲ መዋቅሮች ወደፊት ሴቶች በአመራር ውስጥ ያላቸው ውክልና ወደ 50% እንዲያድግ ተጨባጭ ውጤት የሚያመጡ ስልቶችን የመቀየስና የእቅድ አካል አድርገው የመንቀሳቀስ ኃላፊነት አለባቸው፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ሴቶች በአመራር ምደባ ውስጥ በየእርከኑ የሚኖራቸው ውክልና ከ30% ሊያንስ አይገባም፡፡
3. በየደረጃው የሚገኙ የፓርቲ መዋቅሮች ወጣቶች በአመራር ውስጥ ያላቸው ውክልና እንዲያድግ እቅድን መሰረት ባደረገ መልኩ ተገቢውን ጥረት ማድረግ አለባቸው፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 የተመለከተው ቢኖርም ወጣቶች በወረዳ ደረጃ ከ50% በታች እንዲሁም በዞን ደረጃ ከ25% በታች ውክልና ሊኖራቸው አይገባም፡፡

## አንቀጽ 35

## የአገልግሎት ዘመን

1. አንድ አመራር በአንድ የአመራር እርከን በጠቅላላ ሊያገለግል የሚችለው ቢበዛ ለአሥር አመት ብቻ ይሆናል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ በአንድ አመራር እርከን የአገልግሎት ዘመኑን የጨረሰ አመራር ያካበተውን ልምድና እውቀት ለመጠቀም ሲባል ባገለገለበት የአመራር እርከን ማዕረግ በአማካሪነት ተመድቦ ሊሰራ ይችላል፡፡

## አንቀጽ 36

## መመሪያውን ስለማስፈጸም

1. ይህን መመሪያ በየደረጃው ያሉ አስተባባሪ ኮሚቴዎች፣ የፓርቲ ጽ/ቤቶች እና ሌሎች ኃላፊነት የተሰጣቸው አካላት በተሟላ ሁኔታ መፈጸም እና ማስፈጸም ይኖርባቸዋል፡፡
2. ከዚህ መመሪያ ጋር በሚቃረን መልኩ የአመራር ምደባ ማከናወን ወይም መመሪያው እንዳይፈጸም ማድረግ በፓርቲው የዲሲፕሊን አፈፃፀም መመሪያ መሠረት እንደጥፋቱ ሁኔታ እየታየ ከቀላል እስከ ከባድ የዲስፒሊን ቅጣት ያስከትላል፡፡
3. አንድ አመራር በሀሰተኛ መረጃ የማይገባውን ምደባ ማግኘቱ ሲረጋገጥ ወዲያውኑ መዳቢው አካል ከኃላፊነት እንዲነሳ ያደርጋል፡፡

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ስለራሱ ወይም ስለሌላ እጩ አመራር ሀሰተኛ መረጃ በማቅረብ የአመራር ፕሮፋይልን ወይም መዳቢውን አካል ያዛባ አመራር በፓርቲው የዲሲፕሊን አፈፃፀም መመሪያ መሠረት ተጠያቂ ይሆናል፡፡
5. የብልጽግና ፓርቲ ዋና ጽ/ቤት በየደረጃዉ የአመራር ምደባ አፈፃፀም ሂደትን ለማረጋገጥና ተጠያቂነትን ለማስፈን የሚያስችል ስርዓት የመዘርጋት ኃላፊነት አለበት፡፡

## አንቀጽ 37

## መመሪያውን ስለማሻሻል

ይህ መመሪያ በማንኛውም ጊዜ በፓርቲው የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ሊሻሻል ይችላል፡፡

## አንቀጽ 38

## መመሪያው ስለሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ በፓርቲው የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ከፀደቀበት _______ ቀን 2015 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡